# ረዢሙ ጉዞ - በተቃዋሚነት ወደ ፊት!!

- ከሐብዴድ ወደ ደኢሕዴሕ - ድሮ
- ከደኢሕዴሕ ወደ አማራጭ ሃይሎች - ቀጥሎ
- ከአማራጭ ወደ ኢማዴፌፓ - ቀጥሎ
- ከኢማዴፌፓ ወደ ኢዴሃሕ - 1997
- ከኢዴሃሕ ወደ ሐብዴድ - ጥቅምት 1998
- ከሐብዴድ ወደ ኢማዴፌፓ - አሁን ጥር 1998
- ከኢማዴፌፓ ወደ ?? - ወደ ፊት

ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ቀጣይነት ባለው መልኩ የተለያዩ ሀገራዊ የተደራጁ ተቃዋሚ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን እየመሩ ይገኛሉ። ከላይ የተዘረዘሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ በአንድ ወቅት ወይንም አሁንም የዶክተሩን ብልህ አመራር ያገኙ ናቸው። ከነዚህ ድርጅቶች ውስጥ በአንፃራዊነት የተሻለ ውጤት ያስመዘገበው በዝርዝሩ መጀመሪያ እና ወደ መጨረሻ ላይ የተመለከተው ሐብዴድ ብቻ ነው። ሌሎቹማ ከከሕኮ በስተቀርⵆ ምንም ብርቱ ጥረት ቢያደርጉ ለፓርላማ ወንበር እንኳን አልታደሉም። ምስኪኖች።

እኚሁ ዶክተርⵆ በብልህ አመራራቸው ሌላው ቀርቶ ለፓርላማ ወንበር ያላበቋቸውን ሌሎቹን ምስኪን የፖለቲካ ድርጅቶችንና ጥምረቶችን ለራሳቸው ስምና ምናልባትም የሌሎችን ፍላጎትና ደህንነት ለማስጠበቂያነት ይፈልጓቸዋል። ለምሳሌ አሁንም የኢዴሃህ ሊቀመንበር እና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ እየሠራሁ ያለሁት እኔ ነኝ ብለው ይከራከራሉ። ሆኖም ግን አሁን በተግባር የሚታየው የዶክተሩ ፖለቲካዊ ውክልናⵆ ዕይታ እና ተሳትፎ በኢዴሃሕ አባል ድርጅቶችም ይሁን በሌሎቹ መሐል ላይ በሚገኙትና እርሳቸው በሚመሯቸው ድርጅቶችና ጥምረቶች የጋራ ሥምምነት እና ፍላጎት ሳይሆንⵆ በራሳቸው ልዩ ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆኑን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች በይፋ እየታዩ ነው። ወደ ነጥቦቹ ከመግባቴ በፊትⵆ አንባቢ በደንብ እንዲረዳው በኢዴሃሕ ውስጥ የዶ/ር በየነን አሠላለፍ ላስቀድም።

ዶ/ር በየነ አሁንም የኢዴሃህ አባል የሆኑት 1ኛ) የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረት እና 2ኛ) የኢትዮጵያ ማሕበረ ዴሞክራሲ ፌዴራል ፓርቲ (ኢማዴፌፓ) ሊቀመንበር ናቸው። ይህ ሁለተኛው ኢማዴፌፓ የአማራጭ ሃይሎች ምክር ቤት የሚባለውን የተካናⵆ ከተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች በተውጣጡ ግልሠቦች አባልነት በ1997 ዓ.ም. የተቋቋመ ህብረ-ብሔር ፓርቲ ነው። ከዚህ በተጨማሪምⵆ ዶ/ር በየነ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት መስራች አባል የሆነው የሃዲያ ብሔረሠብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ( ሃብዴድ) ሊቀመንበር ናቸው።

ወደ ምርጫ 1997 ስንመለከት፤ ዶ/ር በየነ በዋነኛነት የምርጫ ቅስቀሳ እና ክርክር ያደርጉ የነበሩት በኢዴሃሕ ስም ነበር። በጊዜው ይህን ማድረጋቸው ትክክለኛ እና አግባብነት ያለው አካሄድ ነበር። በራሳቸው ንዑስ ክልል ሳይገደቡ በየቦታው እየሄዱ ሕዝብ ኢዴሃሕን እንዲመርጥ በመቀስቀሳቸው በዕርግጥም የኢዴሃሕ ሊቀመንበር መሆናቸውን አሳይተዋል። ሕዝቡም በጊዜው ተቀብሏቸው ነበር።

ከምርጫው በኋላ፤ በተለይም ወደ ፓርላማ የመግባትና ያለመግባትን አስመልክቶ፤ የተደረገው ምክክርና ውሳኔ እንዲሁም ዛሬም ቢሆን ውሳኔውን አሳማኝ ለማድረግ እየቀረበ ያለው ማስረጃ ግን ከላይ ከተጠቀሰው የቅድመ ምርጫ ሃላፊነት ጋር የማይገናኝና ችግርም ያለበት ሆኖ ይገኛል።

ሰሞኑን፤ ጥር 27 ቀን 1998 ዓ.ም. በአዲስ አበባ በተካሔደው የኢማዴፌፓ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ ይህንኑ ያለፈ የፓርላማ የመግባት ውሳኔና በኢዴሃሕ ውስጥም ያስከተለውን ልዩነት አስመልክቶ ውይይት ተደርጎ ነበር። በዚህ ውይይት ወቅት፤ በመጀመሪያ ደረጃ ዶ/ሩ የኢዴሃሕ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ (ሰባት ለሶስት በሆነ) ወደ ፓርላማ እንግባ የሚል ውሳኔ ማሳለፉን ሀሰት ነው ይላሉ። ሆኖም ግን በውጪ ያሉ ሰባት ድርጅቶች መግባታችንን ሲቃወሙ፤ በሀገር ውስጥ ያሉ ሶስቱ ሁኔታውን አይተው ለመግባት፤ ሁለቱ ደግሞ ሌላ የተለየ አቋም እንደወሰዱ ያምናሉ። ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በጋራ ለመወሰን ይጠባበቁ እንደነበር፤ ነገር ግን **ከቅንጅት በጊዜ መልስ** ስላልተገኘ **«ተንሳፈን እንዳንቀር ስንል»** ገባንም ብለው ያስረዳሉ። በሌላ አግባብ ደግሞ፤ **«ባለብን ህጋዊና ፖለቲካዊ ሃላፊነት ምክንያት ወደ ፓርላማ ለመግባት የተወሰነ (በቂ ያልሆነ) ምክክር በማድረግ ወስነናል»** ይላሉ። በተለይም ደግሞ ከውሳኔያቸው በፊት ወደ መረጣቸው አካባቢ ሁለት ጊዜ እንደተጓዙና ህዝቡም **«መች ነው ፓርላማ የምትገባው?»** ከማለት ባሻገር **«አትግባ»** እንዳላላቸው በማስታወስ ውሳኔያቸው ትክክል መሆኑን ያብራራሉ። በርሳቸው ብልህነት የተሞላበት ፓርላማ የመግባት ውሳኔ የመረጣቸው ሕዝብ በ1992 ዓ.ም. ከደረሰበት ዓይነት **ዳግም ሥቃይና ዕልቂት የዳነ** መሆኑን ዶክተሩ ሲያስረዱ፤ ከአስተያየት ሠጪዎች አንዱ ውሳኔው በመጀመሪያ ሰሞን በሕዝቡ ውስጥ ጥያቄ ያስነሳ ቢሆንም አሁን ግን ትክክለኛ መሆኑን ህብረተሠቡ እንደተረዳውና፤ ይልቁንም አሁን የአካባቢው ሕዝብ ከመንግስት የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን (ለምሳሌ የግብር ቅነሳና ስረዛ) እያገኘ መሆኑን ከአሞ ሸለቆ የመጡ ተወካይ አስረድተዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የምክክርና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች እና በመጨረሻም ተገኘ የተባለው ውጤት በአጭሩ ዶ/ሩ በተለያየ ደረጃ ያለባቸውን ሃላፊነት ከግንዛቤ ያላስገባ፤ ነገር ግን በሃላፊነት ቅደም ተከተል በመጨረሻ ደረጃ ያለውን **እሳቸው እንደሚሉት** የራሳቸውን ምርጫ ክልል ሕዝብ ፍላጎት በዋነኛነት ያካተተ መሆኑን ያሳያል። በመሠረቱ፤ ነፃነት ወዳዱና የትግሉ

ፈር ቀዳጅ የሆነው የሃዲያ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየና የተለሳለሰ ዐቋም ይኖረዋል ብሎ ማመን ያስቸግራል። የከምባታ ሕዝብም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም።

ያም ሆነ ይህ፤ በውሳኔው ሂደት የኢዴሃሕ ምክር ቤት የሰጣቸውን ትልቅ ሀገራዊ የፖለቲካ ሃላፊነት እና ውሳኔ አላስፈፀሙም። ውሳኔው በአደረጃጀቱ ህብረ-ብሄራዊ የሆነው (ነገር ግን አሁንም ራሳቸው በሊቀመንበርነት የሚመሩት) የኢትዮጵያ ማሕበረ ዴሞኪራሲ ፌዴራል ፓርቲም ውሳኔ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። በሀገር ውስጥም ካሉት የአንጋፋው የደቡብ ሕብረት አባል ድርጅቶች (አሁንም በርሳቸው የሚመራ) የጋራ ፍላጎት እና ስምምነት አልተደረሰበትም። በኢዴሃሕ/ደኢህዴሕ ዓርማ ስር ወደ ምርጫ ገብተው ያገኙትን የሕዝብ ድምፅ በኢሕአዴግ ተቀምተው ተቃውሞ በማሰማት ላይ የሚገኙትን የጌዲኦ፤ የዳውሮ፤ የወላይታ፤ የደቡብ ኦሞ፤ የአሞቲክ፤ የሲዳማ፤ ወዘተ ብሔረሠቦችና አካባቢያዊ ፓርቲዎች ሳይመክሩበት፤ በምርጫው **አሸንፈዋል** የተባሉትን የከምባታና የሃዲያ ዞን ተወካዮች ብቻ ወደ ፓርላማ በዶ/ሩ **ትዕዛዝና** መሪነት የገቡ በመሆናቸው ውሳኔው የደቡብ ሕብረትም የጋራ ውሳኔ አይደለም። በዚህ የዶክተር በየነ የግል ውሳኔና አካሔድ የተበሳጩ አንዳንድ የደቡብ ሕብረት አባል የሆኑ የብሔረሠብና የአካባቢ የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸውን ከሕብረቱ በማራቅ ላይ ይገኛሉ። ለነገሩ የከምባታ ሕዝብ ኮንግረስ ሊቀመንበር የሆኑት ግለሠብ «ዶ/ር በየነ በስልክ፤ **ወስደህ ሰዎችህን ፓርላማ አስመዝግብ** ብሎ ባዘዘኝ መሠረት ነው ያስፈፀምኩት።» ሲሉ የተደመጡ በመሆኑ ውሳኔው በሁለቱ ድርጅቶች አመራር እንኳን የጋራ ምክክር የተደረገበትና ይሁንታ ሳይደረስበት ዶክተሩ በግላቸው ያሳለፉት መሆኑን መገመት አያዳግትም። ይህ የተሳሳተ ውሳኔ የህዝብ ዕምነትን ያሳጣቸው አንዳንድ የሐብዴድ እና ከሕኮ አመራር አካላት ምሬታቸውን በግልፅ እየተናገሩ በመሆኑ የውሳኔው ባለቤትና ለደረሰውም ኪሳራ ተጠያቂው ዶክተሩ ናቸው። ሆኖም ግን ማንም ደፍሮ ጠያቂ ሊሆን እስካሁን አልቻልም።

ስለሆነም፤ ዶ/ር በየነና ሌሎች በኢሕአዴግ ፓርላማ የገቡ ግለሠቦች የሚወክሉት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረትን ሳይሆን፤ ከዚያም ዝቅ ሲል የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ሕብረትን ወይንም የኢትዮጵያ ማሕበረ ዴሞክራሲ ፌዴራል ፓርቲን ሳይሆን፤ በአግባቡ የሚወክሉት በሃዲያ እና በከምባታ ዞኖች ውስጥ የሚገኙትንና የእነርሱን ፓርላማ መግባት **የደገፉትን** የሕዝብ ክፍሎችን እንደሆነ መታወቅ አለበት። ከላይ ለማሳየት እንደሞከርኩት፤ ወደ ፓርላማ የመግባት ውሳኔውን እነሱ ከሚሉት በተለየ የሰፊውን የሐዲያና የከምባታ ሕዝብን ይሁንታና ፍላጎት ያላገናዘበ ከሆነ አሁንም ግለሰቦቹ የሚወክሉት የመረጣቸውን ሕዝብ ሳይሆን ራሳቸውን መሆኑንና፤ ኢሕአዴግም እየተደራደርኩ ነው ማለት የሚገባው ከዶ/ር በየነ ጋር እንጂ ከሌላ አለመሆኑን ሊገነዘብ ይገባዋል።

ከላይ የተቀመጠውን ሁኔታ ግልፅ ማድረጉ በአንድ በኩል እነሱ (እነ ዶ/ር በየነ) የሌላቸውን ውክልና አለን ብለው እናዳያስቡ ሲረዳ በሌላ በኩል ደግሞ ኢሕአዴግ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት ጋር፤ ወይንም ከደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲዊ ሕብረት

ወይንም ህብረ-ብሔር ከሆነው ከማሕበረ ዴሞክራሲ ፌዴራል ፓርቲ ጋር ፤ አልፎም ከሐብዴድ እና ከከምባታ ሕዝብ ኮንግረስ ጋር እየተደራደርኩ ነው በማለት ፕሮፖጋንዳ እንዳይሰራበት ለማስጠንቀቅ ነው።

ይህንን ጥያቄ ቀድሞ ለማምከን ዶክተሩ በቅርቡ የኢማዴፌፓን ጠቅላላ ጉባኤ በተቀነባበረ መልኩ በመጥራት አሁንም የዚሁ ፓርቲ ሊቀመንበር ተደርገው ተሰይመዋል። ይኸው የአንድ ቀን በጥንቃቄ የተጠራ ስብሰባ የታቀደለትን ዓላማ፤ በአንድ በኩል ለዶክተሩ ዕውቅና በመስጠት እና በሌላ በኩል ደግሞ የደቡብ ሕብረትን በዘዴ የማፍረስ ጅምር በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል። ሐገራችን አሁን ባለችበት አስቸጋሪ ሁኔታ፤ የሕዝብን ፍላጎት ያገናዘበ አዲስ የአጭር ጊዜ መርሀግብር የሌለው፤ ነገር ግን በምናውቃቸው ብልህና ዘላቂነት ባለው መልኩ የሚንቀሳቀሱ እነ ዶ/ር በየነን በመሰሉ (እስቲ እናንተ ሞክሩት ማለት የማይፈልጉ) ዜጎች የሚመራ ፓርቲ ችግርና ሥቃያችንን ከማራዘም በዘለለ ለነፃነታችን መረጋገጥ ምንም ፋይዳ የለውም። ይህ ዕውነትነት እንዳለው በየደረጃው በሂደት የምናየው ይሆኖል፤ ሆኖም ግን የአካሔዱን ተስፋ አስቆራጭ ውጤቶች በቅርቡ ማየትና መስማት የምንጀምር ስለመሆኑ አልጠራጠርም።

የአንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የሥራ አፈፃፀም መለካት ያለበት ፓርቲውን ወደ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት ለማድረስ በመቻሉና ባለመቻሉ እንጂ፤ ፓርላማ ተቀምጦ እስከመቼውም በታማኝ ተቃዋሚነት የሕዝብን ድምፅ በማስተጋባቱ አይደለም። ይሄንንማ የሌላው ሲቪል ማሕበረሠብ አካል በመሆን ከፓርላማ ውጪ ሆኖ ማከናወን ይቻላል። ውጤት ማምጣት ያልቻሉ የፓርቲ መሪዎች ከምርጫ በኋላ ሃላፊነት ሲያስረክቡ በብዙ ሀገሮች አይተናል። የኛዎቹ ግን ይህን ቢያውቁም አያደርጉትም። ለውጥ ካላደረግን ደግሞ ውጤት ሩቅ ናት፤ ብትገኝም የዕውነት ውጤት አትሆንም። ሰዎቹ በባህሪያቸው ያው ናቸውና።

ሌሎች በደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲዊ ሕብረት ታቅፈን የነበርን የብሄረሠብና አካባቢያዊ ፓርቲዎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ማሕበረ ዴሞክራሲ ፌዴራል ፓርቲ አባል ልንሆን ቀርበን የነበርን ከሁሉም አካባቢ (ሐዲያና ከምባታን ጨምሮ) የመጣን ነፃ ኢትዮጵያውያን ቀልዱን ትተን በሀገራዊ የሕዝብ ትግል ውስጥ አካል ሆነን ለመቀጠልና ግዴታችንን ለመወጣት፤ ዕምነታችንን የሚያራምድ ወደ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ የሥልጣን ባለቤትነት፤ ዘላቂ ሠላምና ልማት የሚወስደንን መሪ ፓርቲ ሳይዘገይ ማፈላለግና መወገን ወይንም እንደ አዲስ መፍጠር አለብን።

**የፍላጎታችን ጣሪያና የትግሉ ግብ የግብር ቅነሳ ወይንም ስረዛ አይደለም። ታማኝና ዘላቂ ተቃዋሚነትም አይደልም።**

ብዙ በንቲ